በእንተ ምጽዋት [በአበው ትምህርት]

1. ምጽዋት ምንድነው?

2. ስንመጸውት የሚቀበለን ጌታችን ስለመሆኑ

3. ውዳሴ ከንቱና ምጽዋት

4. ምጽዋትን እነማን ይስጡ?

5. እንደ አቅማችን ልንመጸውት እንደሚገባ

6. ምጽዋትን ለእነማን እንስጥ?

7. ይልቁኑ ምጽዋትን ለእነማን እንስጥ?

8. ምጽዋት የመስጠት ቅደም ተከተል

9. እንዲህ ላለውስ ምጽዋትን መስጠት ይገባል?

ምጽዋት ምንድነው?

☞ "ምጽዋትስ አምላካዊ ብድር ናት፣ ይህችውም የታመነችና የምትረባ አምላካዊ ንግድ ናት። ብልህ ሰው ከፈጣሪው ከእግዚአብሔር ዘንድ የሚያኖራት አደራ ናት። በነባቢት መቅደስ ዘንድ ተቀባይነት ያላት ቍርባን ናት። እግዚአብሔርም ስም አጠራሩ ከፍ ከፍ ይበልና መሥዋዕትን ያይደለ ምጽዋትን እሻለሁ አለ። ሆሴ.6:6፤ ማቴ.9:13 [ፍትሕ መንፈሳዊ አንቀጽ.16]

☞ ምጽዋት ማለት የዕለት ምግብና ያመት ልብስ ለቸገራቸው ሰዎች ገንዘብ መስጠት ነው። ደግሞም ምክር ለቸገራቸው መምከር፤ ትምህርት ለቸገራቸው ማስተማር ምጽዋት ነው። እንዲያውም በጠቅላላው ለሰው የቸገረውን ሁሉ ማድረግ ምጽዋዕት ይባላል። [ጎሃ ጽባህ ገጽ.42: ብላቴን ጌታ ኅሩይ ወልደ ሥላሴ]

☞ መስጠትም ለመጽደቅ ነው። እገሌ የታላቁ፣ የእገሌ ልጅ ነው። ታላቅ ነገር ልስጠው፣ እገሌ ግን የታናሽ (የድሃው) የእገሌ ልጅ ነው፤ ትንሽ ነገር ልስጠው እገሌም ጻድቅ ነው፤ መልካሙን ይውሰድ አትበል፤ ይህን የሚያደርግ ኃጢአተኛ ነው፤ የተናቀውን ይውሰድ፣ ይህ ይሰጠኝ የነበረ ወዳጄ ነው፣ ታላቁን እሰጠዋለሁ፣ ለዚህ ግን አላውቀውምና ትንሽ እሰጠዋለሁ፣ ይህን ሁሉ አትበል። አንተስ ለልጆቹ ደግ እንደሆነ አባት ገንዘብህን ክፈል። ለቸገረው አብዛለት፤ ላልቸገረው ግን አሳንስ እንጂ ሥራህ ነው እንጂ የጻድቅ ጽድቁ ወደ አንተ አይመጣም፤ የኃጢአተኛም ኃጢአቱ አያገኝህምና፣ [ርቱዓ ሃይማኖት ገጽ.105]

ስንመጸውት የሚቀበለን ጌታችን ስለመሆኑ

☞ ወንጌል እንዲህ ይላል:- "ጻድቃንም መልሰው ይሉታል። ጌታ ሆይ፥ ተርበህ አይተን መቼ አበላንህስ? ወይስ ተጠምተህ አይተን መቼ አጠጣንህ?... ንጉሡም መልሶ። እውነት እላችኋለሁ፥ ከሁሉ ከሚያንሱ ከእነዚህ ወንድሞቼ ለአንዱ እንኳ ስላደረጋችሁት ለእኔ አደረጋችሁት ይላቸዋል።" ማቴ.25:45

☞ **ታሪክ 1**- በቁስጥንጥንያ የነበረ በመመጽወቱ ልዩ የሆነ አንድ ሰው ነበር። እርሱ በከተማው ጎዳና ሲዘዋወር ለድሆች ከመጸወተ በኋላ እንዳያውቁትና ምስጋናቸውንም ላለመስማት ፈጥኖ ከነርሱ ይሄድ ነበር። አንድ ወዳጁ እንዴት እንዲህ ለጋስ ሊሆን እንደቻለ በጠቀው ጊዜ አንድ ቀን በቤተ ክርስቲያን ካህኑ 'ለድሆች የሚመጸውት ለክርስቶስ ነው የሚሰጠው' ብለው ሲያስተምሩ ሰማሁ "ይህማ እንዴት ይሆናል? ክርስቶስ በሰማያት ያለ አይደለምን?" በማለት ለማመን ተቸገርኩ። ከዕለታት ባንዱም ቀን ወደ ቤቴ እየሄድኩ ሳለ አንዱ ነዳይ ሲለምን ከራሱ ላይም የክርስቶስ ፊት ሲያበራ አየሁ። አንድ መንገደኛም ጥቂት እንጀራን በሰጠው ጊዜ ጌታ እጁን ዘርግቶ እንጀራውን ተቀብሎ የሰጠውንም ሰው ሲበባርከው ተመለከትኩ። ከዚያች ጊዜ ጀምሮ በነዳያን ራስ ላይ የክርስቶስ ፊት ሲያበራ እመለከታለሁ። ስለዚህም በታላቅ ፍርሀት የሚቻለኝን ልግስና አደርጋለሁ።" በማለት ተናግሯል። [ከምስራቃውያን አባቶች አንዱ]

☞ **ታሪክ 2**- ገና የአሥራ ሁለት ዓመት ልጅ ሳለሁ የቅዳሴ ጸሎት ልካፈል በሐዋርያው የቅዱስ ቶማስ ቤተ ክርስቲያን ተገኘሁ። አንድ አረጋዊ ካህን ለሕዝቡ የእግዚአብሔርን ቃል ያስተምር ነበር። በትምሕርቱ መካከል ስለምጽዋት ሲናገር 'ማንም ሰው ለተቸገረ የሚያደርገው ሥጦታ የጌታችን የተቀደሱ እጆች ላይ እንደማስቀመጥ ነው' ሲል ሰማሁት። የሰማሁት በጣም አስደነቀ። ለመሆኑ ጌታችን በክብር ያረገና በአባቱ ቀኝ የተቀመጠ ሆኖ ሳለ በምድር ለአንድ ችግረኛ የሚሰጥን ምጽዋት እንዴት ሊቀበል ይችላል? የማይመስል ነገር ነው። እንዴትስ እንዲህ ያለ የሐሰት ትምህርት ይሰጣል? ስል አረጋዊውን የእግዚአብሔር ሰው ተቸሁት። የሰማሁትን በኅሊናዬ እያሰላሰልኩ ወደ ቤቴ ስመለስ በመንገድ ላይ አንድ እጅግ የተጎሳቆለ ችግረኛ ተመለከትኩ። በሚደንቅ ሁኔታ ጌታችን ቆሞ ይታያል። አንድ ደግ ሰው ወደ ችግረኛው ሰው ቁራሽ ዳቦ ሊሰጠው ቀረበ። ሊሰጠውም እጁን ሲዘረጋ ጌታችን ቅዱሳት እጆቹን ዘርግቶ ዳቦውን ተቀብሎ ካመሰገነው በኋላ በድሀው እጆች ላይ አኖረው። የሆነውን ግን የሚለምነውም ሆነ ምጽዋቱን የሚሰጠው አላወቀም። እጅግ ተደነቅሁ ! ከዚያ ቀን አንሥቶም ማንም ለተቸገረ ወንድሙ እጁን በርኅራሄ ሲዘረጋ በክርስቶስ ቅዱሳት እጆች ላይ እንደሚያስቀምጥ በእርግጥ አመንሁ። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን ሁልጊዜ ከተቸገሩት ሰዎች በላይ ቆሞ ስለማየው ድሆችን ማክበርን ተሞላሁ። ጌታንም እጅግ ደስ እንደሚያሰኘው ስለተረዳሁ በቻልኩት አጋጣሚ ሁሉ ለተቸገሩት የአቅሜን ለማካፈል ተጋሁ። [ራዕየ ኒፎን ገጽ.119-120]

ውዳሴ ከንቱና ምጽዋት

☞ በአንቀጸ ምጽዋት የወንጌል ክፍል ጌታችን እንዲህ አለ **"እንግዲህ ምጽዋት ስታደርግ፥ ግብዞች በሰው ዘንድ ሊከበሩ በምኩራብ በመንገድም እንደሚያደርጉ በፊትህ መለከት አታስነፋ፤ እውነት እላችኋለሁ፥ ዋጋቸውን ተቀብለዋል።"** ማቴ.6:2። በሰማይ ዋጋን እንዳናጣ ከውዳሴ ከንቱ ርቀን ልንመጸውት ይገባል።

☞ ቅዱስ ጳውሎስም እንዲህ አለ **"ለሰው ሳይሆን ለጌታ እንደምታደርጉ፥ የምታደርጉትን ሁሉ በትጋት አድርጉት፥ከጌታ የርስትን ብድራት እንድትቀበሉ ታውቃላችሁና። የምታገለግሉት ጌታ ክርስቶስ ነውና።"** ቆላ.3:23-24

☞ ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ "ስትመጸውት ለሌሎች እንዲያዩህ አትፈልግምና ስለዚህ ነገር አትጨነቅ። ለውዳሴ ከንቱ ብለህ አላደረግህውምና ዓለም ሁሉ እንኳ ቢያወድስህ ማንም አያይህም።ጌታችን "ለሰዎች ትታዩ ዘንድ ምጽዋታችሁን በፊታቸው እንዳታደርጉ ተጠንቀቁ፤" ማቴ.6:1 ብቻ አይደለም ያለው "እንግዲህ ምጽዋት ስታደርግ፥ ግብዞች በሰው ዘንድ ሊከበሩ በምኩራብ በመንገድም እንደሚያደርጉ በፊትህ መለከት አታስነፋ፤" ማቴ.6:2 ለታይታ ስትሉ አታድርጉት ጭምር እንጂ።" ብሎአል። ይህም ስንመጸውት የሰው መኖር አለመኖር ሳይሆን ውዳሴ ከንቱ ፈልገን ነው ወይ የምንመጸውተው? የሚለው የልቡናችን ሃሳብ ነው ሊያስጨንቀን የሚገባው።

☞ ምጽዋትን ሲሰጥ በውዳሴ ከንቱ የሚፈተን መስጠቱ ጨርሶ ካለመስጠት ግን የተሻለ ነው። ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ውዳሴ ከንቱን ሽታችሁ አታድርጉ በማለት ሲያስተምር አንድ ባለጸጋ ወደ ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ቀርቦ "ምጽዋት መመጽወት እወዳለሁ ውዳሴ ከንቱም እወዳለሁ አለው። ውዳሴ ከንቱውን ትተህ መጽውት አለው። አይሆንም ሁሉንም

እወዳለሁ ይህ ከቀረ ምጽዋቱም ይቅር አለው። እንኪያስ አትተው መጽውት ሰው ዘር ይዘራል ባይጠብቀው የእሸት እህል ያጣታልን? አንተም የዚያን ያህል ጥቂት ዋጋ አታጣም ስጥ ብሎታል።" [የማቴዎስ ወንጌል አንድምታ]

እነማን ይስጡ?

☞ **"አንዲትም ድሀ መበለት መጥታ አንድ ሳንቲም የሚያህሉ ሁለት ናስ ጣለች። ደቀ መዛሙርቱንም ጠርቶ። እውነት እላችኋለሁ፥ በመዝገብ ውስጥ ከሚጥሉት ሁሉ ይልቅ ይህች ድሀ መበለት አብልጣ ጣለች።"** ማር.12:43-44 እንዲል ጥቂት እንኳ ያለው ቢኖር ሊመጸውት ይገባል።

☞ ፍትሐ ነገሥት እንዲህ ይላል:- የምጽዋት ረብሀ ጥቅሟ ብዙ ነው፤ እያንዳንዱ እንደተቻለው ይስጥ ባለጸጎችም ነዳያንም። ሁለቱንም የጠቀሰው ከሁለቱ አንዳቸውንም ባይጠቅስ ላለመመጽወት ምክንያት በሆነ ነበርና ሁለቱንም ጠቀሰ በእርሷ በኩል ክብር ማግኘት የሁሉም ድርሻ ነውና። ዋጋዋም እንደሰጭዋ ትጋት መጠን ነው። [ፍትሐ ነገሥት ምን አለ: ገጽ.178]

☞ መተርጉማን በወንጌል አንድምታ በጠበበው ደጅ ግቡ የሚለውን ቃል ሲተረጉሙ "ሰፊ በር ሰፊ መንገድ የተባለ ባለጠጋን መጽውት ድኃን ጹም ማለት ነው። ጠባብ በር ጠባብ መንገድ ባለ ጸጋን ጹም ድኃን መጽውት ማለት ነው" በማለት ጠባብ የተባለው ድሃን መጽውት የሚል ነው ብለዋል።

☞ ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅም "ወንድሜ ሆይ የምጽዋት ነገር ባለጸጋና ታላላቅ ሰዎችን ብቻ የሚመለከት አይደለም ድሆችና የተቸገሩትንም ጭምር እንጂ ምክንያቱም በርሷ ታላቅ ዋጋና ለሁሉ ድኅነት አለና። ኑሮውን በልመና የሚገፋ ሰው ለርሱ ስለ ምጽዋት ማውራት የተገባ ነው። ይህም ሁለት ናስ እንኳ እስኪያጣ የተቸገረ ድሃና ችግረኛ እንደሌለ ነው።" ብሎአል።

እንደ አቅማችን ልንመጸውት እንደሚገባ

ምጽዋት የኃጢአት ሥርየት ምታሰጥ በሰማያት ዋጋ የምታሰጥ ምግባር ስለሆነች ሀብታሙም ድኃው ሊሰጥ እንደሚገባ አይተናል። ከአቅማችን በላይ እስኪሆን ግን ልንጨነቅ አይገባንም።

☞ ቅዱስ ጳውሎስም እንደ አቅማችን ልንሰጥ እንደሚገባ እንዲህ ብሎ ተናገረ "እንደ ዓቅማቸው መጠን ከዓቅማቸውም የሚያልፍ እንኳ ወደው እንደ ሰጡ እመሰክርላቸዋለሁና።" 2 ኛ ቆሮ.8:3

☞ ዳግመኛም ብጹዕ የሚሆን ጳውሎስ እንዲህ አለ:- "በጎ ፈቃድ ቢኖር፥ እንዳለው መጠን የተወደደ ይሆናል እንጂ እንደሌለው መጠን አይደለም።" 2 ኛ ቆሮ.8:12

☞ ፍትሕ መንፈሳዊም እንዲህ ይላል:- "መላ ገንዘቡን ግን መመጽወት ለሰው ሁሉ አልታዘዘም። መጀመርያ መላ ገንዘብን መመጽወት ይገባል ያለው ፍጹም ልትሆን ከወደድክ ገንዘብህን ሁሉ ሽጠህ ለነዳያን ስጥ ብሎ ጌታ ስለተናገረ ነው። [ፍትሕ መንፈሳዊ አንቀጽ 16]።

☞ መጽሐፈ ሐዊ ላይም እንዲህ የሚል አለ:- "ቅዱስ በርሱኑፍዮስ ከተናገረው ቃል የመጣ የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ወዳጅ የሚሆን ከሕዝቡ አንዱ የበርሰኑፍዮስ ደቀመዝሙር የሚሆን አባ ዮሐንስን እንዲህ ብሎ ጠየቀው ሰው ማናቸውንም ነገር ከእኔ ቢፈልግ ባይኖረኝ ተበድሬ ልሰጠው በውኑ ይገባልን? ስለዚህም ነገር መለሰለት ሰው ሰውን ከእጁ የሌለውን ገንዘብ ቢለምነው ተበድሮ ሊሰጥ አይገባውም። አንድ በሽተኛ ምጽዋት ይሰጠው ዘንድ ሐዋርያው ጴጥሮስን ቢለምነው ወርቅ ብር የለኝም ብሎታልና ተበድሮ አልሰጠውምና ገንዘቡ ለዕለት ምግቡ ብቻ ያህል ቢሆን ግን ለሌላ ሊሰጥ አይገባውም እሱ ራሱም አጥቶ ሊያዝን አይገባውም። ሰው ለዕለት ምግቡ ለኑሮው የሚበቃው ገንዘብ ቢያጣ መታገሥም

ባይቻለውለው ለማኝ በለመነውም ጊዜ ቢደነግጥ ቢታወክ የምሰጥህ የለኝም ይበለው እንጂ ሊሰጥ አይገባውም። ሐዋ.3:7 [መጽሐፈ ሐዊ.ምዕራፍ 20 ገጽ.552]

☞ ዳግመኛም በመጽሐፈ ሐዊ እንዲህ የሚል አለ። "ይኸውም ሐሰት አይደለም ከዕለት ምግቡ በቀር ምንም ምን የሌለው ሰው ይሰጥ ዘንድ ነውር ነቀፋ የለበትም ማለት አይገባውም። የአምስቱ የደናግል ምሳሌ አስብ በፋናቸው ላይ ዘይት ይጨምሩላቸው ዘንድ ሰነፎች ብልሆቹን በለመኗቸው ጊዜ ለእኛም ለእናንተም አይበቃም እንዳሏቸው ሐዋርያው ጳውሎስም ስለ ደጎቹ ሰዎች ጽፎ ወደ ቆሮንቶስ ሰዎች በላከው መልዕክቱ ከእናንተ የተረፈውን ለዚህ ጉዳይ መሙሊያ ይሁን ብሎ እንዳሳሰበ። 2 ኛ.ቆሮ 8:10-11፤ ማቴ.25:8-10:: [መጽሐፈ ሐዊ ምዕራፍ 20 ገጽ.552]

☞ በአንድ በኩል የፍጽምና ደረጃ ላይ የደረሱ አበው ያላቸውን ሸጠው ከዚህ አልፈው ራሳቸውን ሸጠው ሲመጸውቱ በስንክሳር ተጽፎ ስናነብብ የደረሱበትን የብቃት ደረጃ ማሰብ ይገባናል። እኛ በመስጠታችን ብዛት የቅዱሳኑ ገድል እንዳንታበይ ልጓም የሚሆን ፍጹም ለመሆን ከወደድንም በግብር እነርሱን ልንመስል እንደሚገባ የሚያስተምር ሕያው ወንጌል ነው። እኛ ቅዱሳኑ ከደረሱበት የብቃት ደረጃ ሳንደርስ በእነርሱ ልክ የፍጹማንን ሕግ ለመፈጸም መሞከር በራሱ ፈተና አለው። መንፈሳዊ ልምምድን በጥቂት በጥቂቱ እንጂ በአንዴ የሚደረስበት አይደለምና።

☞ ከዚህ ውጪ መሠረታዊ ፍላጎታችንን ካሟላን ባልንጀሮቻችን ነዳያንን እንደ ራሳችን አድርገን ልንወዳቸው ይገባናል። ከአቅም በላይ መስጠት ከሕግ በላይ ማድረግ ትሩፋት ሆኖ ዋጋ የሚያሰጥ ቢሆንም በደካማ እምነት ያለችንን መጽውተን እግዚአብሔርን ለማማረር ግን ምክንያት ልናደርገው ግን አይገባም።

☞ በመጽሐፈ ሐዊ እንዲህ የሚል አለ:-

"ጥያቄ- አባቴ ሆይ ተርጉምልኝ ንግግርህንም ግለጥልኝ ገንዘቡ ከዕለት ምግቡ የማይተርፍ ቢሆን ሰው እንደሚስማማው ሊሰጥ አይገባውምን እርሱ ራሱ እንዳያዝን ስላደረገውም ነገር እሱ ራሱ በፈቃዱ ስላደረጋት በጎ ሥራ ማዘን እንዴት ይገባል?

መልስ:- ሥራውን ሁሉ ለይተህ በማወቅ ትሠራ ዘንድ ይገባል በጎ ሐሳብንም በልቡናህ ታሳድር ዘንድ ይገባል ከሠራኸውም በኋላ እንዳትታወክ እንዳትጸጸት ሰው ከችሎታው የበለጠ ቢሠራ እርሱ በጎ ሥራን የሚሰራ ቢሆን ወይም የሆነውን ማናቸውንም ቢሆን ሥራውን ለይቶ ካለማወቅ ይቆጠራልና ከዚህም በኋላ ለሚሠራው ሰው ስህተትን መታወክን ያመጣል። ይኸውም ሥራ ክፉ አይደለም ሰው ከጉልበቱ በላይ የማይቻለውን አይደክምምና ነው እንጂ።

[መጽሐፈ ሐዊ ምዕራፍ.20 ገጽ.553]

በፍትሕ መንፈሳዊ አንቀጽ 16 እንዲህ ይላል:- "ምጽዋት ከተሰጠ በኋላ እንዳይጸጸቱ መሆን ይገባዋል። ሰጭውም ምጽዋት በሚሰጠው ሰው ላይ የሚታበይ ያይደለ ሰው ወዳጅ ይሁን"

ከአቅማችን በላይ ለማድረግ ሞክረን በኋላ ላይ እግዚአብሔር ላይ የምናማርር እና የምንጸጸት እንዳንሆን ሲሉ በአቅማችን ልናደርግ እንደሚገባ አበው ይመክሩናል።

☞ በእውነት ከራሳችን ያለፈ ገንዘብ አጥተን ነው ወይ ብለን ስንጠይቅ ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ እንዲህ ሲል ይገስጸናል። " ለአዝናኝ ተዋናዮች እና ዘማውያን ሴቶችን ለማየት ሌሎች የሚሰጡትን አትመለከቱምን? ሌሎች ለአዝናኝ ተዋንያንና ለዘማውያን ከሚሰጡት ግማሹን እንኳ ስጡ። ሌሎች ለዘፋኞች ከሚሰጡት ግማሹን እንኳ ለክርስቶስ ስጡ። ከትዕቢታቸው የተነሳ በአደባባይ ለሚተውኑ የሚሰጡትን ያህል ስንኳ ለተራበው ስጡ። የዘማዊቷን ልብስ በወርቅ ያስጌጣሉ አንተ ግን ክርስቶስ እርቃኑን ሆኖ እያየሀው የክርስቶስን ሥጋ በቁራጭ ልብስ መሸፈን አትፈልግም? በፈቃድህ ባዶ ለሆኑ ነገሮች ገንዘብህን ታባክናለህ ድሃውን ለማልበስ ሲሆን ግን ራስህን የድሆች ድሃ ታደርጋለህ።" በማለት አሳዛኙን የእኛን እውነታ ይገልጸዋል።

☞ በርግጥም ብዙዎቻችን መሠረታዊ ፍላጎታችንን አሟልተን ቅንጦትን ለማድረግ ስለምንወድ ነው የማንመጸውተው። ቅዱስ ጳውሎስ **"አንዳችንም ልንወስድ አይቻለንም፤ ምግብና ልብስ ከኖረን ግን፥ እርሱ ይበቃናል።"** 1ኛ ጢሞ.6:8 ብሎናል። በመቀማጠል የሚኖሩ ሰዎችን መጽሐፍ ቅዱስ ሙታን ነው የሚላቸው **" ቅምጥሊቱ ግን በሕይወትዋ ሳለች የሞተች ናት።"** 1ኛ ጢሞ. 5:6

ምጽዋትን ለእነማን እንስጥ?

"ለሚለምንህ ሁሉ ስጥ" ሉቃ.6:30 እንዲል ለሁሉም እንድንሰጥ ጌታችን አዞናል።

"እኔ ግን እላችኋለሁ፥ በሰማያት ላለ አባታችሁ ልጆች ትሆኑ ዘንድ ጠላቶቻችሁን ውደዱ፥ የሚረግሙአችሁንም መርቁ፥ ለሚጠሉአችሁም መልካም አድርጉ፥ ስለሚያሳድዱአችሁም ጸልዩ፤ እርሱ በክፎዎችና በበጎዎች ላይ ፀሐይን ያወጣልና፥ በጻድቃንና በኃጢአተኞችም ላይ ዝናቡን ያዘንባልና።" ማቴ.5:44-45 እንዲል የእግዚአብሔር ልጅነታችን የሚታወቀው ያለ አድልዎ ስንመጸውት ነው።

☞ በእረኛው ሔርማ [Shepherd of Hermas] ላይ እንዲህ የሚል አለ:- "እግዚአብሔር ከሰጠህ ከእጆችህ ፍሬ መልካም ሥራን አድርግ በየዋሕነት ያለ መጠራጠር ለተቸገሩት ሁሉ ቀድሞ ትሰጣቸው ለነበሩትና ላልነበሩትም ሁሉ ስጥ። እግዚአብሔር ስጦታው ለሁሉ እንዲደርስ እንደሚወደው አንተም እንዲሁ አድርግ። የሚቀበሉትም ለምንና በምን ምክንያት እንደተቀበሉት በእግዚአብሔር ፊት መልስ ይሰጡበታል። ተቸግረው የወሰዱ ፍርድ የለባቸውም። በሐሰት ምክንያት የተቀበሉት ግን ፍርድ አለባቸው።ስለዚህም ምክንያት ሰጪው ወቀሳ የለበትም። ምክንያቱም እርሱ ከእግዚአብሔር እንደተቀበለ ግዴታውን በየዋሕነት ያለ ጥርጥር ለተገባውና ላልተገባው ሁሉ ሰጥቷልና። [እረኛው ሔርማ]

☞ ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅም እንዲህ አለ:- "ምጽዋትን ለባልንጀሮቻችን ወይም በእምነት ለሚመስሉን ብቻ ልናደርግ አይገባም ለማያምኑም ጭምር እንጂ። በሕገ ኦሪት የወደቀ አህያን ብታገኝ የማን እንደሆነ ሳትጠይቅ ከወደቀበት ታነሳዋለህ። ይህ ለእንስሳት ማድረግ ያለብህ ኃላፊነት ከሆነ እንደምን አብልጠን ያለ ልዩነት ሰዎችን ለሰዎች ልናስብ ይገባን ይሆን?"

☞ በመጽሐፈ ገነት [Book of Paradise] ላይም እንዲህ የሚል አለ "አንድ አባት ልብሱን ለአንድ ድሃ ይሰጠዋል። ቅርጫትን ይዞ ለመሸጥ ምግብንም ለመግዛት ወደ ገበያ በወረደ ጊዜ አንዲት ዘማዊት የርሱን ልብስ ለብሳው ያያታል። እጅግ ተናደደ አለቀሰም:: እግዚአብሔር ሊያስተምረው ከሃሳቡም ሊያሳርፈው መልአክን ላከለት። የእግዚአብሔር መልአክም ተገልጦ "አትዘን ለድሃው ልብስህን በሰጠህበት ቅጽበት ልብሱን ክርስቶስ ለብሶታል። ከዚህ በኋላ ስለሆነው ያንተ ኃላፊነት አይደለም።" አለው።

ምጽዋትን በሰጠንበት ቅጽበት ዋጋችንን እግዚአብሔር እንደሚሰጠን በማሰብ ምጽዋትን የሚቀበለውን ሰው ልንመራመር አይገባንም። በሰው ልቡና ያለውን የሚያውቅ እግዚአብሔር ብቻ ነውና።

ይልቁኑ ምጽዋትን ለእነማን እንስጥ?

☞ ምንም እንኳ ምጽዋትን ለሁሉም የምናደርገው ቢሆንም መጽሐፍ ቅዱስ ግን ልናስቀድም የሚገባውን ይነግረናል።

ቅዱስ ጳውሎስ "እንግዲያስ ጊዜ ካገኘን ዘንድ ለሰው ሁሉ ይልቁንም ለሃይማኖት ቤተ ሰዎች መልካም እናድርግ።" ገላ. 6:10።

ዳግመኛም ቅዱስ ጳውሎስ እንዲህ አለ "ነገር ግን ለእርሱ ስለ ሆኑት ይልቁንም ስለ ቤተ ሰዎቹ የማያስብ ማንም ቢሆን፥ ሃይማኖትን የካደ ከማያምንም ሰው ይልቅ የሚከፋ ነው።" 1ኛ ጢሞ.5:8 እንዲል በሃይማኖት የሚመስሉንን መዘንጋት

ከማያምነው ሰው የከፋ ነው ይለናል። በአንድ አካል ያሉ ብልቶች ያላቸውን ሊተሳሰቡ ይገባል። አፍንጫ ሲመታ ዓይን ያለቅሳልና::

☞ በፍትሕ መንፈሳዊ አንቀጽ 16 ላይም እንዲህ የሚል አለ:- "ምጽዋት ምንም ለሚሻት ሁሉ የምትገባ ብትሆንም ከሰው ለይቶ ለሰው ሊሰጧት ትገባለች።" ይላል።

☞ርቱዓ ሃይማኖትም እንዲህ አለ:- "ለአንተስ ለሁሉም መልካም ነገርን አድርግ። ይልቁንም ለሃይማኖት ሰዎች። የሃይማኖት ሰዎችም በዋሻው፣ በተራራው በፍርኩታው፣ በምድር ጉድጓድ ያሉ ናቸው። ለእነዚህ ራሳቸውን ላስቸገሩ ገዳማውያን ስጦታን አብዛላቸው፤ በሚመጣው ዓለም በርግጥ ይነግሣሉና። ጻድቃኑም ከርስታቸው ይከፍሉሃልና። ስለ ኃጥአን ግን ጌታ ይከፍልሃል፤ አበድረኸዋልና። ብድርህም ከገንዘብህ መቶ እጥፍ ነው። [ርቱዓ ሃይማኖት ገጽ.105]

ምጽዋትን የመስጠት ቅደም ተከተል

1 ኛ. በሃይማኖት ምክንያት ለታሠሩ ሰማዕታት

2 ኛ.ለካህናት

3 ኛ.ለተቸገሩ ዘመዶች

4 ኛ.ለተቸገሩ ምዕመናን ሁሉ

5 ኛ.ላላመኑ ችግረኞች

☞ ሃይማኖታችንን አንክድም ለጣዖት አንሰግድም ብለው መታሠር መደብደብ ለደረሰባቸው፣ የቤት ቃጠሎ፣ የሀብት ዝርፊያ እንዲሁም ውድመት ለደረሰባቸው ሰማዕታተ ጽድቅ ቅድሚያ ከሰጠን በኋላ

☞ በማስቀጠልም በችግር ውስጥ ሆነው ሰውና እግዚአብሔርን በማገናኘት፣ በማጎሌት፣ በሰዓታት፣ በቅዳሴ፣ በማጥመቅ፣ በማቁረብ፣ የበደለኞችን በደል በደስታ ተቀብለው ለሕመማቸው መድኃኒቱ ንስሐን በማቅረብ ያሉ ካህናትን በችግር ምክንያት ቤተሰብ እንዳይጎዳባቸው አገልግሎት እንዳይጓደልባቸው መጎብኘት እንዲገባ ያስረዳል። ግን ከተቸገሩ እንጂ ካህናት ስለሆኑ ብቻ ምጽዋት ሊሰጣቸው ይገባል ማለት አይደለም።

☞ ከዚህም በመቀጠል የተቸገሩ ምዕመናንን መጎብኘትን በቤተሰቦቻችን መጀመር ይገባናል። ይህም አድልዎ አይደለም መቸገራቸውን የሚያውቃቸው ውሎ አዳራቸውን የሚያውቅ የቅርብ ሰዋቸው ስለሆነ እንጂ ። ሲቀጥል ለሰጨ ዘመድ ከመሆናቸው ይልቅ የሚበልጠው የእግዚአብሔር ልጆች መሆናቸው ነውና የእግዚአብሔር ልጅ በመሆን ሁሉም አንድ ስለሆኑ፤ ደግሞም በእነዚህ የሚያቆም አይደለም ፀሐይ ስታበራ ከመስኮቷ እንደምትጀምር መስጠትን ከቤቱ ይጀምር አለ እንጂ፤ በእነዚህ ያቁም አላለምና። ምክንያቱም ከእነዚያ ቀጥሎ ለተቸገሩ ምዕመናን ሁሉ በማለት ሲያጠቃልለው እንመለከታለንና። [ፍትሐ ነገሥት ምን ይላል? የኔታ በጽሐ አለሙ]

በእንተ ምጽዋት [በአበው ትምህርት]

ምጽዋትን እንዲህ ላለውስ መስጠት ይገባል?

☞ በርግጥ የምንሰጠው ሰው ችግረኛ ይሁን አይሁን ላናውቅ እንችላለን። እርሱን መመርመር የእኛ ድርሻ አይደለም። ከእኛ የሚጠበቀውን ከሰጠን መድኃኔዓለም ዋጋውን አያሳጣንም። ይሁን እንጂ በግልጥ ቤተ ክርስቲያን ማታበረታታው ምጽዋት መስጠት አለ።

1 ኛ. ለኃጢአት ተግባር የሚሰጠውን- ለጫት ለሲጋራ ለመጠጥ ብሎ የሚጠይቀንን ሰው ግን መስጠት አግባብ አይደለም። ምጽዋት ምሕረት ማድረግ እንደመሆኑ ሥጋውና ነፍሱን የሚጎዳውን ነገር ለሚያደርግ ሰው አጋዥ መሆን ምሕረት ማድረግ ሳይሆን የጥፋቱ ተባባሪ ያደርገናል ስለዚህ ለእንዲህ ዓይነቱ ምጽዋት ልናደርግ አይገባም። እንዲህ ያለ ሰው ሳይፈልግ ከተያዘበት ሱስ የተነሳ የሚጠቅመውን ባለማወቅ አደንዛዥ እጾችን ቢጠይቀን የሚጠቅመውን መርጠን ግን መመጽወት እንችላለን። የጫት ሲጋራ በሚጠይቁን ፈንታ የእለት ጉርሳቸውን መሙላት እንችላለን ከዚህ በላይ ካሉበት ክፉ ግብር እንዲወጡ ምክራችንን ልንመጸውታቸው እንችላለን።

2 ኛ . ቅዱስ ጳውሎስ እንዳለው **"ደግሞ ከእናንተ ጋር ሳለን። ሊሠራ የማይወድ አይብላ ብለን አዘናችሁ ነበርና።"** 2 ኛ ተሰ.3:10 በማለት እንዳዘዘን መስራት ሲችሉ አቅም ኖሯቸው በስንፍና ምክንያት ሳይሰሩ ከሌላ የሚጠብቁትን ሰዎች ምጽዋትን መስጠት የነርሱን ስንፍና ማበረታታት በኛ ላይ ጥገኛ ሆነው ሁሌም የተረጂነት ስሜት እንዲኖራቸው ማድረግ ነውና ልናበረታታው አያስፈልግም። "ሊሠራ የማይወድ አይብላ" የተባለው ግን ሊሠሩ የማይችሉ ከሆኑት ጋር ልንለይ ይገባናል። ሕጻናት፤ አቅማቸው የደከመ አረጋውያን፤ የአዕምሮ ሕሙማን በደዌ (በሕመም) የተያዙ ሁሉ መሥራት ስለማይወዱ ሳይሆን እንደሌሎች ወጥተው ወርደው ለመሥራት አቅም የሌላቸው መሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል።

☞ ዮሐንስ ክሮንስታድ [Jhon Kronstadt] የተባለ የምስራቅ ሊቅ My Life in Christ በተባለ መጽሐፉ እንዲህ አለ:- "ብዙ ድሆች ለህልውናቸው አስፈላጊ ልብስና መጠለያ አጥተው ባለጠጎችም ከሚገባቸው በላይ ሀብትን ማከማቸታቸው ፍትሐዊ አይደለም። ይሁን እንጂ የሚሰራ (የሚደክም) አብዝቶ ሊያገኝ ይገባዋል ሰነፍ የሆነውም በድህነት በጉስቁልና ሊኖር ይገባዋል። ስለዚህም አንዳንዶች በራሳቸው ከስራ ፈትነትና ከሥንፍናቸው የተነሳ ድሃ እንደሆኑ ብናውቅ በሥራችን (በድካማችን) ያገኘነውን ልናካፍላቸው አንገደድም። ጳውሎስ እንዳለው "ሊሰራ የማይወድ አይብላ" 2 ኛ ተሰ.3:10 ይላልና። በእርጅና ላሉ ፣ በሕመም ላሉ ፣ ለፍተው ዝቅተኛ ደመወዝን ለሚቀበሉ፣ በሕይወታቸው ከባድ ችግር ለገጠማቸው፣ ብዙ ቤተሰብ ኖሯቸው ለተቸገሩ፣ የሚያመርቱት ላነሰባቸው ሁሉ በተለይም ባለጠጋ የሆንን ፈጥነን ልንረዳቸው ይገባናል። በሐዋርያት ጊዜ በነበሩ ታሪኮች በጥንቷ ቤተ ክርስቲያን ምሳሌነት ልንመራ ይገባናል።" ይላል።" [My Life in Christ Book 2, Jhon Kronstadt, page 480]

አዘጋጅ:-ተክለ ማርያም [ጅማ ሐመረ ኖኅ ኪዳነ ምሕረት]